# ፍርደ ገምድል ዳኛ

የዶ/ር አብይ አስተዳደር ወደ ስልጣን ሲመጣ ባብዛኛው ኢትዮጵያዊ ለዘመናት የተራበውንና የተጠማውን ቃላቶች ስላሰማለት መስማት የሚፈልገውን ስለሚናገር ብቻ ሁለት እጁን ዘርግቶ እንደተቀበለው ሁላችንም ያየነው ነው ። እኔም እንደ ብዙሃኑ በንግግሩ ደስተኛ ብሆንም በተግባሩ ግን እምብዛም እስካሁን የተማረኩበት ነገር አላገኘሁም ። ባነጋገሩ ይሄ ጎደለው ባይባልም በተግባሩ ላይ ግን በርካታ ቅሬታዎች አሉኝ ባብዛኛው ህዝብ የፈነጨበት የኤርትራው ስምምነት ነው ፣ እንደኔ ግን የኤርትራው ስምምነት በጣም ያዘንኩበት ስምምነት ነው ፣ የኤርትራው ስምምነት ኢትዮጵያ እንደ ሀገር የአሰብን የይገባኛል ጥያቄ ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ አፈር አልብሶ መጥቷልና ።

ጠ/ሚር አብይ በተደጋጋሚ ስለ ይቅርታ ይሰብካሉ ፣ በሱ ምንም ቅሬታ የለኝም ፣ ሆኖም ግን በአብዛኛው ባለፈው መንግስት ስም እንደ ኢሕአዴግ ይቅርታ ሲጠይቁ ያ የጅምላ ይቅርታ እንጂ በግል እንደ አንድ የኢሕአዴግ ባለስልጣን በነበሩበት ወቅት በግላቸው ስለፈጸሟቸው ተግባሮች በግሌ ደግሞ ይሄን ይሄን በማድረጌ ተፀፅቻለሁ እናም የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ እጠይቃለሁ ሲሉ አንድም መድረክ ላይ አልተሰሙም ። ስለሆነም ከጅምላው ይቅርታ አስቀድሞ የግል ይቅርታ ይቀድም ነበር ብዬ ስለማምን ይቅርታቸውም አደናጋሪ ይቅርታ ነው ብዬ በግሌ አምናለሁ ።

ጠ/ሚሩ በግል ይቅርታ ሊጠይቁበት ይገባል ያልኳቸውን እኔ ከማውቀውና ስህተት ነው ብዬ ከማምነው ተግባራቸው ባለፈው ጽሁፌ ማለትም July 30, 2018 [“ከራስ ጋር መታረቅ”] በሚለው ጽሁፌ ላይ ስላሰፈርኩት እዚህ ላይ መድገሙ አላስፈላጊ መስሎ ስለታየኝ የቀደመውን ፅሁፌን ወደኋላ ሄዶ ማየት ይችላል ።

ወደተነሳሁበት ርዕስ ስመለስ ጠ/ሚሩ በተደጋጋሚ ይቅርታን ሲሰብኩ ይቅርታው ሁሉን አቀፍ እንደሚሆን ተናግረዋል ፣ ይህ ማለት እከሌ ከከሌ ሳይለይ ማለት እንደሆነ እረዳለሁ ፣ ሆኖም ግን በተግባር የምናየው ያ ሲሆን አይደለም ።

በቅድሚያ አንባቢያን የፍርዱን አካሄድ እንዲያስተውሉ እንጂ ያንዱ ስርዓት ደጋፊ የሌላው ስርዓት ተቃዋሚ በመሆን ያቀረብኩት እንዳልሆነ አንባቢ ሊገነዘብልኝ ይገባል ።

ባለፈው ሳምንት የቀድሞው ጠ/ሚር አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ ባልሳሳት የዶ/ር አብይ መንግስት ተወካይ በመሆን ዚምባዌ የሚደረገውን መንግስታዊ ምርጫ በታዛቢነት ፍትሃዊ ምርጫ መካሄዱን ለማየት መሄዳቸው ይታወቃል ። ይህ በንዲህ እንዳለ አቶ ኃይለማርያም ከጠ/ሚሩ ታዘው ይሁን በግል ፈቃዳቸው ባላውቅም ከቀድሞው መሪ ኮሎኔል መንግስቱ ኃይለማርያም ጋር በመኖሪያ ቤታቸው ተገናኝተው እንደተጨዋወቱ የሚያሳይ አብረው የተነሱትን ፎቶ አሳይተውናል ። መልእክቱ ምንም ይሁን ምን ፣ አሁን ያሉት ጠ/ሚር አብይ የቀድሞው መሪ ኮሎኔል መንግስቱ ኃይለማርያም ከፈለጉ ወደ ሃገራቸው ሊገቡ ይችላሉ ብለው ሲናገሩ ተደምጠዋል ፣ ይህ ማለት እንግዲህ ምህረቱ ኮሎኔል መንግስቱንም ያጠቃልላል ማለት ነው ። አሁን ደግሞ በቀድሞው መሪ የበታች ሹማምንት ሆነው ያገለግሉ የነበሩ ለ27 ዓመታት በኢጣልያን ኢምባሲ በጥገኝነት ይኖሩ የነበሩ ኮሎኔል ብርሃኑ ባይህ እና ሌተናል ጀነራል አዲስ ተድላ በዘር ማጥፋት ወንጀል ስለተከሰሱ ምህረቱ እነሱን አይመለከትም ማለት ምን ማለት ነው ? ዋናው መሪያቸው ይቅር ተብሎ ጀሌዎቹ ይቅርታው አይመለከታችሁም የሚለው የመንግስት አቋም ሊዋጥልኝ አልቻለም ።

ዛሬ በህይወት ያሉ የቀድሞው የደርግ ባለስልጣናት መሀከል ተፈርዶባቸው ፍርዳቸውን ጨርሰው የወጡ ፣ ሳይፈረድባቸውም ሆነ ተፈርዶባቸው ነገር ግን ሳይያዙ ከሀገር የወጡ እንዳሉ ይታወቃል ፣ ታዲያ ፍርዱንም ጨርሶ ከወጣው ሳይያዝም አምልጦ ከወጣው ሁሉ የነዚህ ሁለት ግለሰቦች ወንጀል በውን ከሌሎች ሁሉ ወንጀል በልጦ ነው? እነሱን በዘር ማጥፋት ወንጀል ስለተከሰሱ ምህረቱ አይመለከታቸውም የተባለው ? ወይንስ ጉዳዩ ግላዊ ይሆን ? እንደኔ ግንዛቤና አመለካከት ይሄ ፍርደ ገምድልነት ነው ብዬ አምናለሁ ።

በተረፈ አንባቢ የራሱን ግንዛቤ ሊወስድ ይችላል ።

ታዛቢው

August 06, 2018